# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 194 ጥር 24 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በታሪክ ነፃ የሚወጡ መሆናቸውን እየተናገሩ፤ በታሪክ ነፃ አውጭነት ተስፋ አድርገው ወደ እስርና ሰቆቃ የሚጋዙ ወገኖቻችን ጥሪ እረፍት ሊነሳን ይገባል ይላል። ኃላፊነት ይሰማን ይህንን ግፈኛ ሥርዓት አስወግደን በየእለቱ እየደረሰብን ያለውን ውርደት ለማስቆምና ወገኖቻችንን ለማዳን እንፍጠን።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7: የሶስተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ። ጉባኤውንም አስመልክቶ መግለጫ አወጣ

ግንቦት7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ለአንድ ሳምንት ያካሄደውን ሶስተኛ አመታዊ ጉባኤውን ባለፈው ቅዳሜ ጥር 19፣ 2004ዓ/ም ምሽት በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቁን ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መግለጫ አስታወቀ። በተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚኖሩ አባላት በተወካዮቻቸው አማካይነት በተሳተፉበት በዚህ ጉባኤ ላይ ቁጥራቸው ከሶስት መቶ በላይ የሆኑ ተወካዮች መገኘታቸውን የጉባኤው አዘጋጆች ከሬዲዮ ክፍላችን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል። በኢትዮጲያ ውስጥ ያሉት የተለያዩ ክልሎች ተወካዮች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳትፈውበታል በተባለው የግንቦት 7 ሶስተኛ ጉባኤ ከአውስትራሊያ፤ ከኒውዚላንድ፤ ከአፍሪካ፤ ከሩቅና መካከለኛው ምስራቅ ፤ ከአውሮፓ፤ ከሰሜን አሜሪካና ከካናዳ በርካቶች እንደተሳተፉ ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ጉባኤ አዘጋጆቹ መረጃ አብዛኛው የንቅናቄው አባላት በየሚኖሩባቸው አገሮች የንቅናቄውን አላማ ከግብ ለማድረስ እንዲረዳ ተብሎ በተዘጋጀው ረቂቅ የስትራቴጂ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ላይ በስፋት ከመወያየታቸውም በላይ ንቅናቄው ባለፈው አንድ አመት ያከናወናቸውን የሥራ ሪፖርቶች አዳምጠው በጥንካሬዎችና ድክመቶች ላይ ግልጽና ጥልቅ ውይይት አድርገዋል።

ለአንድ ሳምንት ያህል ጊዜ ሲካሄድ የነበረው ይህ የግንቦት 7 ጉባኤው ባለፈው ቅዳሜ ( ጥር 19/2004) ምሽት ሲጠናቀቅ ባወጣው የጋራ መግለጫ፤ ግንቦት 7 ለኢትዮጵያዊያን ተስፋን የፈነጠቀ፤ በወያኔ ላይ ደግሞ ስጋትን ያሰፈነ ድርጅት መሆን ቢችልም ዘረኛውንና ግፈኛውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድና በምትኩም ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈኑባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እስካሁን ካከናወናቸው ተግባራት እጅግ የላቀ ሥራ መሥራት እንዳለበት መላው አባላቱ እንደሚገነዘቡት ተገልጿል።

በማስከተልም አገራችንና ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጋ ከዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃ የማውጣትና ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈኑባት ሃገር የመገንባት ከፍተኛ ኃላፊነት በእኛ ትውልድ ላይ የወደቀ መሆኑን ተረድተናል ካለ በኋላ ፤ አባላቱ ይህንን እውን ለማድረግ ህይወታቸውን፣ ንብረታቸውንና ጊዜያቸውን ለትግሉ ለማዋል ቆርጠው መነሳታቸውን ገለጠዋል ብሏል።

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማኅበራት ጋር በጋራ ለመሥራት እየተደረገ ያለውን ጥረት እንደሚያጠናክርም ያስታወቀው የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ኢትዮጵያውያን ለእልህ አስጨራሹ ትግል እንዲቃለቀሉት ጥሪ አቅርቧል።

ግንቦት 7 ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 4 ላይ ያንብቡ።

## ነባር የህወሃት አባላት የሆኑት የሠራዊት አዛዦች በመቀሌና በአዲስ አበባ ከሚገነቡ ትላልቅ ዘመናዊ ህንጻዎች የአብዛኛው ባለቤቶች መሆናቸው ታወቀ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ከትናትና በስቲያ ዜና ዘገባው እንዳስታወቀው በአዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶችና በመቀሌ ከተማ ውስጥ ከተሰሩትና ገና በግንባታ ላይ ከሚገኙ ረጃጅም ህንጻዎች አብዛኛዎቹ በመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ በከፍተኛ አዛዥነት ሥልጣን ላይ ያሉ የቀድሞ ህወሃት ታጋዮች ንብረት መሆናቸው ለማወቅ ተችሎአል።

ኢሳት በግንባታ ላይ ከሚገኙ በርካታ ፎቆች ለአብነት ያህል የጥቂቶቹን በፎቶግራፍ አስደግፎ ይፋ ያደረገ ሲሆን እያንዳንዱ ግንባታ የሚፈጀውን የገንዘብ መጠን ከባለሙያ በተገኘው አሃዝ አስደግፎ አጋልጦአል።

የኢሳት መረጃ ምንጮች እንደገለጹት በተለምዶ ቦሌ መድሀኒአለም እየተባለ በሚጠራው ወይም ወረዳ አስራ ሰባት ውስጥ በምእረባዊያን የቤት ደረጃ የሚሰሩት ቤቶች 90 በመቶ የሚሆኑት የወያኔ የጦር ጄኔራሎች በራሳቸው ወይም በቤተሰባቸው የያዙት ነው።

የሁሉንም ህንጻዎች ባሌቤትነት ለይቶ በማወቅ መረጃውን ለህዝብ ይፋ ለማድረግ በጥረት ላይ ያለው ኢሳት እንደገለጸው፤ ጄኔራል ወዲ አሸብር የተባለው የህወሃት የቀድሞ ታጋይ በሶኮልላንድ ኩባንያ የሚሰራ ባለአራት ፎቅ ህንጻ እያስገነባ መሆኑ ሲታወቅ ለደህንነት ሲባል ማንነቱን ለመግለጽ ካልተፈለገ ህንጻ ተቋራጭ በተገኘው መረጃ ግንባታው አሁን ባለበት ደረጃ 34 ሚሊዮን ብር እንደፈጀና ቀሪው ሥራ ሲጠናቀቅ 55 ሚሊዮን ብር እንደሚደርስ ለማወቅ ተችሎአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በአምባገነኑና ዘረኛው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ድርጅታዊ መዋቅር እርካታ ያላገኙ የፌደራል ፖልሲ አባላት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን በገፍ እየለቀቁ መሆኑ ተዘገበ። በድርጊቱ የተደናገጡት ባለሥልጣናት ሥራቸውን እየለቀቁ የሚወጡትን ፖሊሶች ማሳደድና ማሰር ጀምረዋል

እያንዳንዷን የተቃውሞ እንቅስቃሴ በጉልበትና በጠመንጃ ሃይል አፍኖ ለመያዝ ከመቼውም ጊዜ በላይ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን የፌደራል ፖሊሶችን በማሳደድና በማሰር ላይ እንደሚገኝ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት እጅግ በርካታ የፌደራል ፖሊሶች የወያኔውን ዘረኛ አገዛዝ ማገልገል ትተው በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን እየለቀቁ እንደሚገኙና ለዚህ የሚሰጡትም ምክንያት በሰራዊቱ ውስጥ በሰፈነው ዘረኛ መዋቅር ተማረርው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

በሥርዓቱ ዘረኝነት ተማረው ሥራቸውን በፈቃዳቸው እየለቀቁ ያሉ ፖሊሶች ብዛት ባለፈው አንድ ወር ብቻ ከአንድ መቶ መብለጡን በፈደራል ፖልስ ውስጥ ያሉ ታማኝ ምንጮች ይናገራሉ።

የፈደራል ፖልስ አባላት በብዛት ሥራቸውን ጥለው መኮብለል መጀመራቸውን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሳተላይ ቴሌቪዝን ባለፈው ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ/ም ባቀረበው ዜና ዘገባው እንደገለጸው ምንም እንኳን ለጊዜው በትክክል የታሰሩ ፖሊሶችን ቁጥር ማወቅ ባይቻልም፣ በእየ ክፍለሀገሩና በማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ውስጥ በርካታ ፖሊሶች ታስረው እንደሚገኙ ምንጮች አረጋግጠዋል ብሏል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በሶሪያ ህዝባዊ አመጽ ተጋግሏል፤ ቀጣዩ ኢትዮጵያ ነው ተብሏል

በሶሪያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ ተጋግሎ ቀጥሏል። የአረብ ሊግ የሶሪያው ፕሬዚዳንት አሳድ ስልጣን እንዲለቁ ያቀረበው ሃሳብ በአሳድ ተቀባይነት ያገኘ ባይሆንም የፀጥታው ም/ቤት ጠንከር ያለ መግለጫ አስተላልፏል።

እንደሚታወቀው በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ ንቅናቄ በርካታ ትንግርቶችን እያሳየን ነው። የቱኒዚያን ቢን ዓሊ አቧሯል፤ የግብጹን ሞባረክን በሥልጣን አውርዶ አሁን በቃሬዛ ፍርድ ቤት እየተመለለሱ ናቸው። የሊቢያው ጋዳፊ ሥልጣን አለቅም ብለው በማንገራገራቸው ወጣት ሊቢያውያን በተደበቁነት ጉድጓድ ጎትተው አውጥተው ገድለዋቸል፤ ልጆቻቸው ከፊሎቹ ተገድለዋል፤ ከፊል ተሰደዋል፤ አንዱ ተይዞ ፍርድ እየጠበቀ ነው።

በጎረቤታችን የመንም አሊ አብደላ ሳልህ ለብዙ ወራት ሥልጣን አለቅም ብሎ ቢያንገራግርም አሁን ተገዶ እንዲለቅ ተደርጓል። አሁን ደግሞ ህዝባዊ አመጹ ሶሪያ ውስጥ የአሳድን አገዛዝ እየነቀነው ነው።

ይህ ህዝባዊ አብዮት ቀጥሎ የሚያመራው ወደየት ነው? የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን እያነጋገረ ሲሆን አገራችን ኢትዮጵያ የዚህ አብዮት ቀጣይ መዳረሻ እንደምትሆን የብዙዎች ግምት ነው። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ይህንኑ በመፍራት ቀዳዳዎችን ለመድፈን ጋዜጠኖችን ሳይቀር በሽብርተኝነት ከሶ እያስፈረደባቸው ቢሆንም ይህ አፈና አብዮቱን እንደማያስቀረው ተንታኖች ይናገራሉ።

## ወያኔ ያወጣው አዲሱ የከተማ ቦታን ወደሊዝ የማዛወር አዋጅ በመላው አገሪቱ ውስጥ ታላቅ ተቃውሞ እየቀሰቀሰ መሆኑ ተዘገበ

ሥልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ የከተማ ቦታን በመሸጥ ከፍተኛ የሆነ ሃብት ሲያግበሰብስ የኖረው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ ነባር ይዞታዎችን ወደ ሊዝ ስሪት ለመለወጥ ያወጣው አዋጅ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞን በህብረተሰቡ ውስጥ መፍጠሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች አሰባስቦ የላከው መረጃ አመለከተ።

ከ20 አመት በፊት በባራባሶ ጫማ ቤተመንግሥት ድረስ ዘልቀው ሥልጣን የተቆናጠጡ የወያኔ ባለስልጣናት በቀድሞ መንግሥት ይዞታ ሥር የነበሩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎት መሥጫ ድርጅቶችን ሳይቀር ወደግለሰብ ይዞታ በሺያጭ ለማዛወር በሚል ሰበብ እራሳቸው ወደ አቋቋሟቸው የንግድ ድርጅቶች አዛውረው ካበቁ ቦኋላ የተቀረውን ከነርሱ ጋር ሽርክና ላላቸው ታማኞች በርካሽ ዋጋ ማከፋፈላቸውን የሚያስታውሱ የህብረተሰቡ ክፍሎች፤ በተለይ የአዲስ አበባን ከተማ ለመቆጣጠር ተብሎ በርካታ ቤቶች እንዲፈርሱ እንደተደረገና ቦታው ለባለሃብቶች ሲቸበቸብ እንደነበረ በምሬት ይናገራሉ።

ወያኔ አሁን ያወጣው አዲሱ የሊዝ አዋጅ ቤቶችን በማፍረስና በአዳዲስ የጊዜው ሃብታሞች በማስያዝ የተረፉትን የከተማ ቦታዎችን በሊዝ ሥም ለመውረስና ባለይዞታዎችን ለማፈናቀል የወጣ ነው ተብሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## "ታሪክ ነፃ ያወጣኛል!"

የዳኝነት ካባ የለበሱ የመለስ ዜናዊ ካድሬዎች፣ ፍርደ ገምድል ብይኖችንና ቅጣቶችን በማንበብ ሥራ ላይ ተጠምደው ሰንብተዋል።

በወጣት ጋዜጠኞች፣ በራሱ በወያኔ ደንብ መሠረት የተቋቋሙ የፓለቲካ ፓርቲዎች አመራር አባላት በሆኑ የነፃነት ታጋዮች እንዲሁም ቅን አሳቢዎች በሆኑ ወገኖቻችን ላይ ተላለፈ የተባለውን ወያኔያዊ ብይንና ቅጣት፣ ካባ የለበሱት ካድሬዎች እየተንቀጠቀጡም ቢሆን አንብበውታል።

የመለስን አገዛዝ በጋዜጣ ጽሁፍ እንኳን መቃወም ከአስራ አራት ዓመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ካድሬዎቹ ዳኞች ባነበቡት ጽሁፍ አማካይነት ተነግሮናል።

በመለስ ዜናዊ ህግ ለመቀጣት የተቃውሞ ሃሳብን መግለጽ ወይም አለመግለጽ፤ በጋዜጣ ላይ መፃፍ ወይም አለመፃፍ፤ የተቃውሞ ሰልፍ መጥራት ወይም አለመጥራት ልዩነት እንደማያመጣም አይተናል። አንዳች ነገር ያድርግም አያድርግም መለስ እንዲቀጣ የሚፈልገው ሰው "ፍርድ ቤቱ" እንደሚቀጣው በዓይኖቻችን ያየነው ሃቅ ነው። "አቃቤ ህግ" በሚል ስያሜ የቆመው የመለስ ዜናዊ ተወካይ "አጥፍቷል" ያለው ሰው ሁሉ፤ ፍርድ ቤቱም "አዎ አጥፍቷል" ብሎ ይወስናል። በዚህ ሁኔታ መከራከር፣ ምስክር መቁጠር ዋጋ የለውም። በስህተት "ችሎት" እየተባለ የሚጠራው ቦታ የመለስ ዜናዊ የግል ውሳኔዎች ማንበቢያና ማሳወቂያ አዳራሽ ነው።

ያም ሆኖ ግን በአንዳንዶቹ ውሳኔ ማሳወቂያዎች አድማጮችን ፈገግ ለማሰኘት ሲባል የገቡ የንባብ ማሳመሪያዎች ነበሩ። ለምሳሌ በአንዱ የውሳኔ ንባብ አቃቤ ህግ በስድስት ተከሳሾች ላይ "ከጥርጣሬ በዘለለ በቂ ማስረጃ ሊያቀርብ ባለመቻሉ ነፃ ናቸው" የሚል ተሰምቷል። አቃቤ ህግ "ከጥርጣሬ የዘለለ" ማስረጃ በማን ላይ ኖሮት ነው በስድስቱ ላይ ያጣው? ቀድሞውንስ አቃቤ ህግ መቼ ማስረጃ ማቅረብ አስፈልጎት ያውቃል። ሲያሻው ምስክሮችን እዚያው አዳራሽ ውስጥ ሲያስጠናቸው ይታይ የለምን?

"ችሎት" የሚሰኘው የመለስ ዜናዊ ውሳኔ ማሳወቂያ አዳራሽ ውስጥ የሚደረገውን መታዘብ እጅግ አሳዛኝ ነው።

- አገራችን ወደየት እየሄደች ነው?
- ህግና ፍትህ እንደዚህ ተዋርደው እስከ መቼ እንቆያለን?

እስከ መቼ ይህንን እየታዘብን እንኖራለን?

ባለፈው ሳምንት፣ ይህን በመሰለ አሳዛኝ ድራማ እና አንጀትን የሚቦረቡር የበደልና የጥቃት ስሜት ውስጥ ሳይጠበቅ የፈነዳ አንድ ነጓድጓዳማ ሃቅ ነበር።

የዳኝነት ካባ የለበሰው ካድሬ የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ፍርደ ገምድል ውሳኔ አንብቦ እንደጨረሰ ከተበዳዮች አንዱ የሆነው አቶ ዘርይሁን ገ|እግዚአብሄር

***እኔ ጥፋተኛ አይደለሁም አንድ ቀን ታሪክ ነፃ ያወጣኛል!!!!***

ሲል ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ።

ይህች አንዲት ዓረፍተ ነገር በዚያች እለት ብቻ ሳይሆን በዚያ ችሎት ውስጥ በተከታታይ ሳምንታት ሲነበቡ የቆዩ ብይኖችንና ቅጣቶችን ሁሉ አረከሰች፤ በጥቃት ለቆለሱ አንጀቶችም ማስታገሻ ሆነች።

አዎ! እውነት ነው ዛሬ በመለስ ዜናዊ ችሎት ጥፋተኛ የተባሉ ዜጎች አንድ ቀን ታሪክ ነፃ ያወጣቸዋል። በመለስ ዜናዊ "ችሎት" "ጥፋተኞች" የተባሉ ወገኖቻችን በህዝብ ዓይን ዛሬም ነፃ ናቸው፤ በህዝብ ችሎት ዛሬም ጀግኖች ናቸው። ዛሬ በእነሱ ላይ የፈረዱ፤ ነገ ይፈረድባቸዋል።

በእርግጥም ታሪክ ወገኖቻችንን ነፃ ያወጣቸዋል፤ በክብር ሰገነትም ውስጥ ያኖራቸዋል። ይህ ምንም የማያጠራጥር ሃቅ ነው።

ይሁን እንጂ በደል እየደረሰባቸው ያሉ ወገኖቻችን የሚጠይቋቸው ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉ።

- መቼ ነው ታሪክ ወገኖቻችንን ነፃ የሚያወጣው?
- ታሪክን ራሱ ማነው የሚሰራው?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚሠራው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ብሎ ያምናል። ዛሬ በመለስ ዜናዊ ግፈኛ አገዛዝ ወደ ወህኒ እየተወረወሩ እና ሰቆቃ እየተፈፀመባቸው ያሉት ወገኖቻችን ታሪክ ነፃ እንዲያወጣቸው እኛ ታሪክን መሥራት ይኖርብናል ብሎ ያምናል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በታሪክ ነፃ የሚወጡ መሆናቸውን እየተናገሩ፤ በታሪክ ነፃ አውጭነት ተስፋ አድርገው ወደ እስርና ሰቆቃ የሚጋዙ ወገኖቻችን ጥሪ እረፍት ሊነሳን ይገባል ይላል። ኃላፊነት ይሰማን ይህንን ግፈኛ ሥርዓት አስወግደን በየእለቱ እየደረሰብን ያለውን ውርደት ለማስቆምና ወገኖቻችንን ለማዳን እንፍጠን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

……………………………………………………………………………………………………………………

## ነባር የህወሃት አባላት የሆኑት የሠራዊት አዛዦች በመቀሌና በአዲስ አበባ ከሚገነቡ ትላልቅ ዘመናዊ ህንጻዎች … (ከገፅ 1 የዞረ)

ኮሌኔል ታደለ የተባለ ሌላ የቀድሞ ህወሃት ታጋይም እንዲሁ በአዲስ አበባ ከተማ ታወቂ በሆነው ካልዲስ ካፌ በሚገኝበት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 በ30 ሚሊዮን ብር ተመሳሳይ ፎቅ በማስገንባት ላይ እንዳለ እስከነፎቶግራፉ ለህዝብ እይታ ያቀረበው ኢሳት በተመሳሳይም፤ ጀኔራል ዮህንስ የተባለ ሌላ የቀድሞ ህወሃት ታጋይም እንዲሁ 45 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጎ አንድ ግዙፍ ህንጻ በማስገንባት ላይ እንደሚገኝ አጋልጦአል።

በመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ባለው ግልጽ የዘረኝነት መስፈርት በትውልድ ሃረጋቸው የህወሃት አባላት ለመሆን ያልቻሉና በተወለዱበት ዘር ኮታ ከውትድርና ሹመቱ ለመቋደስ ከበቁት ታማኝ ሎሌዎች አንዱ የሆነው ጀነራል ባጫ ደበሌ 12 ሚሊዮን ብር የፈጀ መለስተኛ ህንጻ አስገንብቶ ለእነ ኤቢሲ የመኪና አክራይ ድርጅቶች አከራይቶ እንደሚገኝ ይፋ ሆኖአል።

የወያኔ የጦር ጀኔራሎች የሚያስገነቡትን ህንጻዎች ማንም ሰው ፎቶግራፍ እንዳያነሳቸው የጥበቃ ሰራተኞችን በማሰማራት በጥብቅ እያስጠበቁት እንደሆነ ይፋ ያደረገው ኢሳት እንደገለጸው፤ ጉዳዩን በቅርበት ከሚከታተሉት ኢንጂነሮች ከተገኘው መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው፣ በቦሌ መድሀኒአለም ፊት ለፊት እና በቦሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጎን የሚሰሩት ከ4 ፎቅ ጀምሮ ያሉት ህንጻዎች ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት በህወሀት ጀኔራሎች ስም፣ ወይም በቤተሰቦቻቸው የሚሰሩ ናቸው።

እነዚሁ ታማኝ ምንጮች እንደገለጡት የአብዛኞቹ ህንጻዎች ዝቅተኛ ዋጋ 45 ሚሊዮን ብር ሲሆን፣ ከፍተኛው ደግሞ 95 ሚሊዮን ብር ይደርሳል ተብሎአል።

ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋራጮች እና መሀንዲሶች የቤቶችን ባለቤትነት በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ ለውጭ ሰዎች እንዳይሰጡ ከፍተኛ ክትትል ይደረግባቸዋል፤ በአካባቢው ፎቶ ግራፍ ለማንሳት ወይም የተለየ ጥያቄ ለመጠየቅ የሚደፍር ሰው ሲቪል በለበሱ የደህንነት ሀይሎች ተይዞ ለምርመራ ይወሰዳል እንደ ኢሳት መረጃ ምንጮች።

ጀኔራል ወዲ አሸብር፣ ጀኔራል ዮሀንስና ሌሎችም ሲኒየር ጀኔራሎች ተጨማሪ ግዙፍ ህንጻዎችን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ገንብተዋል ያለው ኢሳት በመቀሌ ከተማ የሚገኙት የጀኔራሎቹ ህንጻዎች ደግሞ ለመከላከያ ሚኒስቴር ለጽህፈት ቤትና ለማሰልጠኛነት ተብሎ መከራየታቸውንና ጀኔራሎቹ በአመት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚያፍሱባቸው ለማወቅ ተችሎአል ብሎአል።

ምንም እንኳ ከህወሀት ጀኔራሎች ጋር ሲተያይ እዚህ ግባ ባይባልም፣ የኢህአዴግ ሚኒስትሮችም ከ አንድ ሚሊዮን እስከ 10 ሚሊዮን በሚጠጋ ወጪ የተለያዩ ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶችን እያስገነቡ ነው። አብዛኞቹ ሚኒስትሮች በኮተቤ እና በሲኤም ሲ አካባቢዎች የሚካሄዱ የቤት ግንባታዎችን በባለቤትነት ይቆጣጠራሉ።

አዲስ ዜና ጋዜጣ በ1997ዓ/ም የቀድሞዋ የትምህርት ሚኒስትር ገነት ዘውዴ ፣ የኢህአዴግ የፓርላማ ተወካይና የውሀ ሀብት ሚኒስትር የነበረው ሺፈራው ጃርሶ፣ እንዲሁም የስራና ከተማ ልማት ሚኒሰትር የሆነው ሀይሌ አሰግዴ ዘመናዊ ህንጻዎችን በቶዮታ ጋራጅ እና በብስራተወንጌል አካባቢዎች መገንባታቸውን በስእል አስደግፎ መዘገቡ ይታወሳል።

ከሁሉት አመት በፊት ንቅናቄያችን ግንቦት 7 ባካሄደው የምርመራ ጥናት በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ከ98 በመቶ በላይ የሚሆነውን ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች የተቆጣጠሩት የትግራይ ተወላጆች የህወሀት ነባር ታጋዮች መሆናቸውን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ የቤቶች ግንባታ ላይ የተሰማሩትም ሆነ ከፍተኛ ምዝበራ እያካሄዱ ያሉትም እነዚሁ የህወሀት ባለስልጣናት ናቸው።

አንድ የመከላከያ አዛዥ ወርሀዊ ደሞዝ በአማካኝ 3 ሺ ብር ነው። እንደ ጀኔራል ወዲ አሸብር የመሳሰሉት ጀኔራሎች ምንም ሳይመገቡ፣ የቤት ኪራይ ሳይከፍሉ ወይም እድሜ ልካቸውን ምንም አይነት ወጪ ሳያወጡ የሚከፈላቸውን ወርሀዊ የመንግስት ደሞዝ እንዳለ በባንክ ቢያስቀምጡ፣ ከሚያስገነቡዋቸው ዘመናዊ ህንጻዎች መካከል አንዱን ህንጻ ብቻ ለማስገንባት ቢያንስ ለ150 አመት በህይወት መኖርና ሳያቋርጡ ማጠራቀም ግድ ይላቸዋል ብሎአል ኢሳት በዘገባው።

ከ90 በመቶ ያላነሰው ኢትዮጵያዊ በቀን ከአንድ ዶላር በታች በሆነ ገቢ በሚተዳደርበት አገራችን በርካታ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ምሳ መብላት አልችል ብለው በክፍል ውስጥ እንደሚወድቁ፣ በርካታ ታዳጊ ወጣቶችም አንድ ድንች ብቻ በልተው የከሰአት ትምህርት እንደሚማሩ ፣ መምህራንም ለችግረኛ ተማሪዎች በማህበር ተደራጅተው ገንዘብ በማዋጣት የምሳ መግዣ ገንዘብ እንደሚለግሱ የተለያዩ መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ የግንቦት 7 ድምጽን ጨምሮ በርካታ ሚዲያዎች መዘገባቸው ይታወሳል።

ኢትዮጵያ ለአብዛኛው ህዝብ ሲኦል፣ ለጥቂቶች ደግሞ ገነት እየሆነች መምጣቷን በርካታ ታዛቢዎች ሲገልጡ ቆይተዋል።

በቅርቡ ፋይናንሻል ኢንተግርቲ ባካሄደው ጥናት በኢትዮጵያ በየአመቱ ከ3 ቢሊዮን ዶላር ወይም ከ50 ቢሊዮን ብር ያላነሰ ገንዘብ እየተመዘበረ በህገወጥ መንገድ ከአገር ይወጣል። በአለፉት 9 አመታት ብቻ ከአሥራ አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገንዘብ በወያኔ ባለሥልጣናት ተዘርፎ ከአገር መውጣቱን የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅትን ጨምሮ ታማኝ የሆኑ አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አጋልጠዋል።

# ኢትዮጵያ በባእዳን እጅ ነች!!!

ፋሺስቱ መለስ ዜናዊ እኔ ካልገዛኋችሁ አገሪቷ ትበታተናለች እንደ ሶማሊያም ትሆናለች እያለ ማሚረቱን ሰምተን ነበር። ይህ የባእዳን ድምጽ ነው።ከዚህ ቀደም አገሪቷን ሲገዙ የነበሩ ግዥዎች አንድ ትልቅ አገር ለመፍጠር ሲሉ ህዝቡን በደሉ እንጂ እንደመለስ ዜናዊ ዳር ድንበሯን አፍርሰው፤ መሬቷን ለውጭ ሰዎች ቸብችበውና ነዋሪውን መሬት አልባ አድርገው ትበታተናላችሁ እያሉ ሲያሚርቱ አልተሰሙም። የመለስ ዜናዊ መልክ ድሮ የምናውቃቸውን አገር በቀል አምባገነኖችን አይመስልም። የመለስ መልክ የባእድ ፋሽስት መልክ ነው። አገራችንም ከዚህ ቀደም ዓይታ በማታውቀው በዚህ ባእድ እጅ ወድቃለች።

ሶማሊያ እንዲህ እንደዛሬው በጎሰኞች ተከፋፍላ እርስ በርስ እልቂት ውስጥ ከመግባቷ በፊት በሲያድባሬ አዝማችነት ኢትዮጵያችንን ስትወር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ከሚወጉ ሃይሎች ጋር መቆሙን እናስታውሳለን። በዚያን ወቅት ሲያድባሬ የብዙ ኢትዮጵያዊያንን ደም አፍሷል። ብዙ የአገሪቷን ንብረትም አውድሟል። እንዲያ በሆነ ግዜ መለስ ዜናዊ ከስያድባሬ ጎን ቁሞ ነበር። ዛሬም በሌላ መልኩ በመለስ ዜናዊ አዝማችነት በሶማሊያ ምድር የኢትዮጵያዊያን ደም መስዋእት ሆኖ እየቀረበ ነው። ከዚህ መስዋእት ተጠቃሚው መለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ ብቻ ናቸው እንጂ ኢትዮጵያችን ያገኘችው ጠቀሜታ የለም። የኢትዮጵያዊያኖቹ ወጣት ወታደሮች አስከሬን በሶማሊያ ጎዳናዎች ላይ እየተጎተተ ተተፍቶበትና ተዋርዶ በስማቸው የተገኘውን ዶላር መለስ በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ ሰውሮ እያስቀመጠ በዓለማችን ላይ ሃብታም ከሚባሉ መሪዎች ተርታ ለመሰልፍ በቃ እንጂ እንደ ወጣ የቀረው ወታደርና አገራችን ያተረፉት ነገር የለም። ጀሌዎቹም የድሃውን ልጆች አሰውተው ሲያበቁ በአንዲት ጀንበር ባለ ብዙ ሃብት ባለቤት ሁነው እጅግ በሚያስገርም ቅንጦት ተንደላቀው ሲኖሩ ታዩ እንጂ በኢትዮጵያ ስም የሞተው ወታደርና ቤተሰቦቹ ከድህነት አረንቋ ሊወጡ አልቻሉም።

ባለፈው ሳምንት በሶማሊያ ምድር ብዙ የኢትዮጵያ ወታደሮች በአጥፍቶ ጠፊዎች ተገድለዋል።ከእነዚህ ወታደሮች ሞት በኋላ ኢትዮጵያ ምን እንደምታገኝ አዝማቹ መለስ ዜናዊ አይናገርም። ተናገር ተብሎ በፓርላማ መሰሉ አካል ሲጠየቅም ይሄን የመናገር ግዴታ የለብኝም ብሏል። መለስ ዜናዊ ከህዝብ በላይ እኔ ነኝ ብሎ በጽኑ ስለሚያምን እንጂ የይስሙላም ቢሆን የህዝብ ተወካዮች ለጠየቁት ጥያቄ መለስ መስጠት ዋነኛው ሥራው መሆኑ ጠፍቶት አይደለም። ዜጎች በባእድ ምድር እንዲሞቱ የሚደረግበትን ምክንያት የማስረዳትና የማሳወቅ ግዴታው ሆኖ ሳለ "ግዴታ የለብኝም" ማለቱ ለህዝብ ተወካይ ተብየዎች ያለውን ንቀት የሚያሳይ ነው።

ይኸው ግለሰብ ከአያት ቅደመ አያቶቹ ጀምሮ የወረሰው ኢትዮጵያዊያንን የመውጋትና ደም የማፍሰስ አባዜ አልተው ስላለው ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በሶማሊያ ምድር ሲሰው ተገቢውን ክብር ለመስጠት ፈቃደኛ አይሆንም። አገሩን ወክሎ በጦርነት የወደቀ ዜጋ በመንግስቱ አማካኝነት ማንነቱ ለህዝቡ ተገልጦ ተገቢው ክብር ሊሰጠው ይገባ ነበር። እናትና አባቱም ከልጃቸው መስዋእትነት በኋላ ተገቢው ክብርና ጥቅም ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። መለስ ዜናዊና ዘረኛ ድርጅቱ የተጠመዱበት ዋነኛ ተግባራቸው ኢትዮጵያዊያንን ማዋረድ እና ማሳዘን ስለሆነ በዚህ እንኳ ሊገኝ የሚችለውን ክብር ዜጎች እንዲያገኙ አያደርጉም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ወታደር በወደቀበት ተርስቶ ይቀራል። የሞተላቸውም ዜጎች የወታደሮቹን ውለታ ዋጋ ሳይሰጡት ያልፋሉ። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ያለች ኢትዮጵያ እንዲህ የዜጎች ህይወት ከውሾች ህይወት ባለተሻለ ሁኔታ የሚያልፋበት አገር ነች። ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነንና ሁላችንንም የሚቆጨን እነመለስ ዜናዊ ይሄን የሚያደርጉት ባለማወቅ ሳይሆን ሆን ብለው ለኢትዮጵያዊያን ሃይሎች ካላቸው ጥልቅ ጥላቻ በመነሳት መሆኑን ባሰብን ግዜ ነው።

ይበልጥ የሚያሳዝነንና አገራችንን መቅኖ የሚያሳጣት ይሄን የመሰለ ክፉ ባእድ ኃይል በህዝባችን ጫንቃ ላይ ተጭኖ እያዩና እየሰሙ ባለፈና በሞተ ብላሽ ታሪክ ላይ ግዜያቸውን የሚያጠፉ ወገኖችን ስናይ ነው።ከትላንትናው ጠላት ይልቅ ዛሬ እንደ ተራብ ዘንዶ አፉን ከፍቶ ጎሳን እየለየ ዜጎችን የሚያሰቃየው ሃይል ሊያበሳጨንና ሊያሳስበን ይገባ ነበር። በአንዳንድ አካባቢ ባለፈ ሙት ታሪክ ላይ የሚደረጉ ክርክሮች፤ ጩኸቶችና ወቀሳዎች ለባእዳን ሃይሎች ጉልበት ከመሆን የዘለለ ለነጻነታችን ለምናደርገው ትግል የሚፈይዱት ቁም ነገር የለም።በትላንትናው ታሪክ ላይ እየተነታረኩ ግዜ ማጥፋት የሚጠቅመው መለስና ጀሌዎችን እንጂ ነጻነት ለተነፈገው ህዝብ የሚደረገውን ትግል አይደግፍም።

የትላንትናውን በደላችንና መገፋታችንን ለመነጋገር የሚያስችል መድረክ ሊፈጠር የሚችለው መለስ ዜናዊን የመሰሉ ባእዳን ሃይሎች የአገሪቷን መዋቅሮች በሙሉ በተቆጣጠሩበት ሁኔታ አይደለም። መለስ እንደ ሶማሊያ ትሆናላችሁ እያለ የሚያሚርተው አስቦበትና ተዘጋጅቶበት ነው።ለዚህም የሚመቸውን ሚዲያ በሙሉ ተቆጣጥሮታል። በሚሊዮን ዶላር እያወጣ የነጻነት ታጋዮች ድምጽ ሸክሙ ለበዛበት ህዝብ እዳይደርስ እያደረገ መሆኑን አይናችን አይቷል ጆሮአችንም ሰምቷል። በዙሪያውም ህዝቡን የማያውቁ ብዙ"mercenaries" አዘጋጅቷል። እንዲህ ዓይነት በቀቢጸ ተስፋ የሚደረጉ ክፉ ድርጊቶች ሁሉ ፍጻሜያቸው እንደማያምር መለስ ዓይኑ ከሚያየው ጆሮውም ከሚሰማው እንዳይማር እዝነ ልቦናው በት እቢት ተደፍኗል።የመለስ ወዳጁ ነው ተብሎ የሚነገርለት ሙሃመድ ጋዳፊ እንዲህ እንደመለስ ነበር። የሲሪያው አሳዳም የመለስ ዜናዊ ሌላው መልኩ ነው። ህዝብ ማሸነፉ ላይቀር ብዙ ጥፋት ለማድረስ የማይሞክሩት ነገር የለም። ከሚመዙት ክሮች መካከል የመጀመሪያው ህዝቦች ወደ እርስ በርስ ግጭት እንዲገቡ ማድረግና ሌላ ሶማሊያ በምስራቅ አፊሪካ እንዲፈጠር ማድረግ ነው።ከዛሬ መቶ አመት በፊት የተፈጸመውን እየመዘዙ ንትርክ መፍጠር እለ መለስ ዜናዊ ላቆሙት ግብ መዳረሻ እንደሚሆን ዜጎች ሊረዱት ይገባል። በእውነት ነጻነትን የሚፈልግ ዛሬ መወያየት ያለበት ከመቶ ዓመት በፊት የተፈጸመውን በደል ሳይሆን ዛሬ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል እንዴት እናስቁም በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ መሆን አለበት።

አገሪቷ እንዲህ በባእዳን እጅ ወድቃ ባለችበት ወቅት በሞተ ታሪክ ውስጥ ራሱን ቀብሮ የሚሚገት ሃይል ምን ይባላል? ለጊዜው "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅት አይሰማም" ከማለት ባሻገር ሌላ የሚባል ነገር የለም።

በመጨረሻም ለሁላችንም የምትሆን አገር እንድትፈጠር አስቀድመን ህዝብ የበላይ መሆን የሚችልበት መንገድ እንዲፈጠር እውነተኛ ፍላጎት ካለው ሃይል ጋር አብረን ለመሥራት በቅንነት እንነሳ። የዜጎች መብቶች ያለ ገደብ እንዲከበሩ የሚያደርግ ህግ እንዲፈጠር ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ እናድርግ። ፍትህ ነግሶ ሁላችንንም የሚጠብቅ ህግ ልዕልና ያገኘበት አገር እንዲኖረን የሚፈነቀሉ ድንጋዮችን ሁሉ እንፈንቅል የሚያስኬዱ መንገዶችን ሁሉ እንጓዝባቸው። ከዚህ የሚያቆመን ኃይል ሊኖር አይገባም።ይሄንንም ለህልውናችንና ለክብራችንና ለህዝቦች ሰላም ስንል እናድረገው እንጂ ማንንም ለማስደሰት ስንል የምናደርገው የታይታ ሥራ አይሁን።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ኢትዮጵያ በምትባል አገር ውስጥ የሚኖር ሁሉ ነጻነቱ ተረጋግጦ፤ በዚያች አገር ፍትህ ነግሶና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ ህዝብ ብቻ የበላይ የሆነባት አገር እንድትፈጠር ለማድረግ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ከዚህም የሚያቆመው ምንም ኃይል የለም። ግንቦት ሰባት ውስጥ የተሰባሰብን ሃይሎች ለታይታ ብለን የምንሰራው ሥራ የለም። የምንሰራውን ሥራ ለክብራችንና ለህልውናችን ስንል እናደርገዋለን እንጂ ማንም እንዲያደንቀን ወይም እንዲያመሰግነን ብለን የምንሰራው ሥራ የለም።

**ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## በአምባገነኑና ዘረኛው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ድርጅታዊ መዋቅር እርካታ ያላገኙ የፈደራል ፖልሲ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከዚህ በተጨማሪ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በተለይም በሰሜንና መካከለኛው አፍሪቃ አገሮች ህዝባዊ ማእበል ከተነሳና በርካታ አምባገነኖችንም ጠራርጎ ከወሰደ ወዲህ በኢትዮጵያ አገራችን ተመሳሳይ አብዮት እንዳይቀሰቀስበት ከደረሰበት ስጋትና ፍራቻ በመነሳት ፖሊሶቹን ያለአግባብ ያለምንም እረፍት ለረጅም ሰዓት እንዲሰሩ እያደረጋቸው በመሆኑ ፖሊሶቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጭንቀትና የሥራ መደራረብ ተፈጥሮአል። የፌደራል ፖሊሶችን ወያኔ ሆን ብሎ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች በዜጎች መካከል በሃይማኖት፤ በጎሳ ወይም በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ለሚጭራቸው ግጭቶች እየተላኩ ከህዝቡ ጋር እንዲጋጩና በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲጠሉ ይደረጋሉ እንደውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የፌደራል ፖሊስ ከፍተኛ ኢንስፔክተር ለዘጋቢያችን እንደገለጹት፤ ፖሊሶቹ በየዕለቱ ከተጠመዱበት የረጂም ሥራ ጫና በላይ በሰራዊቱ ውስጥ ያለው ዘርን ማከል ያደረገ አድሎአዊነት እንዳስመረራቸው ለማወቅ ተችሎአል። በፌደራል ፖሊስ ውስጥ ትግርኛ ተናጋሪ ወይም ከወያኔ አባል ድርጅቶች በአንዱ አባል ያልሆኑ የሰራዊቱ አባላት ላይ የሚደርሰው አድልዖ እንዳለ ሆኖ በተለይ አንዱ የፖሊስ አባላት እርስ በርስ እንዲሳለሉ መደረጉ የሁሉንም ፖሊሶች ልብ አሸፍቶአል ተብሎአል። ነባር የህወሃት አባላት የሆኑ የፌደራል ፖሊስ አባላት እራሳቸውን እንደንጉስ በሚቆጥሩበት መስሪያ ቤት፤ ትግርኛ ተናጋሪዎቹ አንጋፋ ህወሃቶች ከራሳቸው ዝቅ አድረገው ከሚመለከቱዋቸው የፓርቲ አባል የሆኑ የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆች ውጪ ያሉትን እንደዜጋ ቀርቶ እንደሰው እንደማይቆጥሯቸው ብዙዎች አማረው ይናገራሉ።

## ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሶስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት የጋራ መግለጫ

ጥር 19 2004 ዓ.ም

እኛ በኢትዮጵያ፣ እንዲሁም በውጭ አገራት ውስጥ በአፍሪቃ፣ በአውስትራሊያ፣ በሩቅና መካከለኛው ምሥራቅ፣ በአውሮፓ እና በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የግንቦት 7 አባላት ተወካዮች፣ ከጥር 12 ቀን እስከ 19 ድረስ ባደረግነው ሶስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የንቅናቄያችንን ሪፖርቶች አዳምጠን በጥንካሬዎችና ድክመቶች ላይ ግልጽና ጥልቅ ውይይት ከአደረግን በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎችን አስተላልፈናል።

የንቅናቄዓችንን ተግባራት በመገምገምና ከሪፖርቶቹም በመነሳት ግንቦት 7 ለኢትዮጵያዊያን ተስፋን የፈነጠቀ፣ በወያኔ ላይ ደግሞ ስጋትን ያሰፈነ ድርጅት መሆን ቢችልም ዘረኛውንና ግፈኛውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድና በምትኩም ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈኑባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እስካሁን ከሠራው እጅግ የላቀ ሥራ መሥራት እንዳለበት ተገንዝበናል።

በተጨማሪም፡ እኛ የግንቦት 7 ሶስተኛ ጉባኤ ተሰብሳቢ አባላት

1. ኢትዮጵያ አገራችንና ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጋ ከዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃ የማውጣትና ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈኑባት ሃገር የመገንባት ከፍተኛ ኃላፊነት በእኛ ትውልድ ላይ የወደቀ መሆኑን ተረድተናል፤
2. ይህም በመሆኑም ህይወታችንን፣ ንብረታችንና ጊዜዓችን ለትግሉ ለማዋል ቆርጠን ተነስተናል፤
3. በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ የፓለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማኅበራት ጋር በጋራ ለመሥራት እያደረግነው ያለውን ጥረት ማጠናከር ያለብን መሆኑን ተረድተናል፤

ድርጅታችንን በማጠናከር የወያኔን ግብዓተ-መሬት ለማፋጠን ቆርጠንና አምርረን ተነስተናል።

ኢትዮጵያ አገራችን በታሪኳ አጋጥሟት በማያውቅ የጠላት እጅ ውስጥ ወድቃለች። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ጊዜ ከተሰጠው በአገራችን ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በረዥም ጊዜም ቢሆን መመለስ የማይቻል ሊሆን ይችላል። አገሪቷ ተከፋፍላ፤ ህዝቧ እርስ በርሱ ተቆራቁሶ፤ ለም መሬቷ የባዕዳን ቱጃሮች መፈንጫ ሆኖ ኢትዮጵያዊያን በገዛ አገራችን ባርነትን እንኳን የምናገኝበት እድል የሌለ በመሆኑ ይህ ዘረኛና ዘራፊ አገዛዝ ጊዜ ሳይሰጠው እንዲወገድ ሁላችንም በጋራ መነሳት እንዳለብን በመገንዘብ ከዚህ የሚከተለውን ጥሪ ለወገኖቻችን እናስተላልፋለን።

1ኛ. በዘረኞች እየተረገጥክ፣ እየታሰርክና ቁም ስቅልህን እያየህ ያለኸው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ገበሬ፣ ሠራተኛ፣ ተማሪ፣ ነጋዴና እና ምሁር፤

2ኛ. በመለስ ዜናዊ ዘረኛ የእዝ አገዛዝ ተቀፍድደህ በአገርህና በወገንህ ላይ እንድትዘምት እየተገደድክ ላለኸው የመከላከያ እና የፓሊስ ሠራዊት፤

3ኛ. ባለማወቅ በውዴታ ወይም በግዴታ በወያኔ ድርጅቶች ውስጥ ታቅፈህ ለግፈኞች ተባባሪ ሆነህ የቆየህ አገር ወዳድ ዜጋ፤

4ኛ. በመንግሥት የሲቪል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለወያኔ የሙያና የእውቀት እገዛ በማድረግ ላይ የምትገኝ ኢትዮጵያዊ፤

ይህን የአገር ማዳን ጥሪዓችንን ስማን። እኛ ግፍ፣ በደል፣ ዘረኝነት በቃን ብለናል። እንተም እንደኛው "በቃኝ!" ብለህ ተቀላቀለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ

ቅዳሜ ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም

## በጋሞ ጎፋ ዞን በጨንጫ ወረዳ አንድ የወረዳው ፖሊስ ለመንፈሳዊ በዓል በተሰበሰበ ህዝብ ላይ በመተኮስ አንድ ሰው እንደገደለና በርካቶችን በጽኑ እንዳቆሰለ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው በጋሞጎፋ ዞን በጨንጫ ወረዳ የሚገኝ አንድ የፖልስ አባል ህዝብ በየአመቱ በድምቀት በሚያከብረው የአስቴርዮ ማርያም በአል ላይ ያልተጠበቀ የተኩስ እሩምታ ከፍቶ አንድ ሰው እንደገደለና ሌሎች ብዙ ሰዎችን እንዳቆሰለ ለማወቅ ተችሎአል።

በእለቱ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ከአርባምንጭ እና ከሌሎች ከተሞች የተሰባሰቡ ሰዎች በአሉን በሚያከብሩበት ወቅት፣ የወረዳው ፖሊስ አባል ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ መሳሪያውን አንስቶ ወደ ህዝቡ በመተኮሱ አንድ ሰው ወዲያው ተገድሎአል። ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎች በጽኑ ቆስለው ሆስፒታል ገብተዋል።

ከፍተኛ የሆነ የህዝብ መተራመስ ተፈጥሮ እንደነበር የገለጸው የኢሳት ዘጋቢ ፖሊሱ በምን ምክንያት ወደ ህዝብ እንደተኮሰ ለማረጋገጥ ባይቻልም፤ እስካሁን ድረስ በቁጥጥር ስር አለመዋሉን ግን ለማወቅ ተችሎአል። በተጨማሪም ተኳሹ ፖሊስ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ መሆኑ እንዲታወቅ ህዝቡ የአካባቢውን ባለስልጣናት በሰላም ተከባብረን እና ተቻችለን በምንኖርበት አገር እርስ በርስ ልታጋጩን አትሞክሩ በማለት ሲቃወም ነበር።

ሀይማኖታዊ በአሉን ለማክበር የተገኘው ህዝብ አጋጣሚውን በመጠቀም በአገዛዙ ላይ ተቃውሞውን ሲያሰማ ውሎአል ተብሎአል።

በጨንጫ ወረዳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመሬት ጋር በተያያዘ የተፈጠረው አለመረጋጋት እንደቀጠለ መሆኑን የኢሳት ዘጋቢ አያይዞ መግለጹን ኢሳት አስታውቆአል።

## በቻይና መንግስት በ200 ሚሊዮን ዶላር በተገነባው አዲሱ የአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ቤትና አዳራሽ ቅጥር ግቢ ውስጥ የዓፄ ሀይለሥላሴ ሐውልት አለመቆሙ፤ በኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራን ዘንድ ቅሬታና ተቃውሞ አስነሳ

ቻይና- ለአፍሪካ ህብረት እንደ ገጸ-በረከት በነፃ ገንብታ ባስረከበችውና ባለፈው ሳምንት የመሪዎቹ ጉባኤ ሲካሄድ ተመርቆ በተከፈተው ታላቅ ህንፃ ውስጥ፤ከፓን አፍሪካኒዝም ሀሳብ አራማጆቹና ከአፍሪካ አንድነት መስራቾቹ ቀደምት የአፍሪካ መሪዎች መካከል ሐውልት የታነፀላቸው፤ የጋናው ኑዋሜ ክሩህማን ብቻ ናቸው።

ሐውልት የታሪክ ምልክት እስከሆነ ድረስ፤ በህብረቱ ጽህፈት ቤት ሐውልት መቆሙ ካልቀረ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል የሚባሉትን የኢትዮጵያውን አፄ ሀይለሥላሴን፤ የግብጹን ጋማል አብድል ናስርን፣ የሊቢያውን ሙአመር ጋዳፊንና የጋናውን ንዋሜ ክሩህማንን ያካተተ አንድ ሀውልት ቢታነጽ፤ ታሪኩን ሙሉና ሚዛናዊ ያደርገው እንደነበር ኢትዮጵያውያን ምሁራን ይናገራሉ።

በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ በተገነባው የህብረቱ አዳራሽ ውስጥ የታነፀው ሐውልት፤ የህብረቱን ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን አስደርገው ግንባር ቀደም ትግል ሲያደርጉ የነበሩትን ቀዳማዊ ሀይለሥላሴን መዘንጋቱ፤ ቁራጭ እውነትን በመስጠት ታሪክን እንደማዛባት ነው ያሉት ምሁራኑ፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ሊገባቸው እንዳልቻለም ተናግረዋል።

በዚህ ዙሪያ ቅሬታቸውን ከገለጹት ምሁራን መካከል ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ይገኙበታል። ፕሮፌሰር ባህሩ፦" በአዲሱ የአፍሪካ ህብረት ህንፃ የንዋሜ ክህሩማንን ሐውልት ብቻ ማቆሙ፤ ለኔ ትርጉሙ አልገባኝም" ነው ያሉት። ፕሮፌሰር መስፍን ደግሞ "ዓፄ ሀይለሥላሴ ያን ጊዜ ባይኖሩ ኖሮ፤ የአፍሪካ ህብረት አሁን የያዘውን ቅርጽ ሊይዝ አይችልም"፤ ብለዋል።

ሁለቱም ምሁራን ዓፄ ሀይለሥላሴ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቋቋምና በህይወት መኖር ከማናቸውም መሪዎች በላይ ያደረጓቸውን አስተዋጽኦ በማብራራት፤ ለንዋሜ ክሩህማን ሀውልት ታንፆ-ሀይለሥላሴ መረሳታቸው እጅግ እንዳስገረማቸው ተናግረዋል። ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉት የኢሳት ምንጮች ግን፤ የዓፄ ሀይል ሥላሴ ሐውልት እንዲቆም ያልተደረገው ፤ዘረኛዉና ባንዳዉ መለስ ሀሳቡን በመቃወሙ እንደሆነ ጠቁመዋል።

መለስ በኢትዮጵያ ታሪክ "ታላቅ መሪ" የመባል በልጓም የማይገታ ልቅ ምኞት አለዉ" የሚሉት ምንጮች፣ ያለፉ የኢትዮጵያ ነገሥታት መልካም ታሪኮችን የማጥፋትና የማጉደፍ ተግባር ላይ ሆኑ-ብሎ የተሰማራዉ፤ ከዚህ 'የግል ስሜቱ' በመነሳት ነው" ብለዋል። በተለይ የዓፄ ሀይለስላሴ ሐውልት በህብረቱ ፅህፈት ቤት መቆሙ፤ ህወሀት ከፍ ያለ ገንዘብ መድቦ የራሱን አዲስ ታሪክ ለማፃፍ የጀመረውን እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃም ሊያበላሽበት እንደሚችል ይገመታል።

በመማሪያ መፃህፍት የፊት ገጾች ከሚወጡት ፎቶግራፉ በተጨማሪ በሚሊዮን በሚቆጠር ገንዘብ በቁልፍ መያዣዎችና በቢል ቦርዶች ላይ ፎቶግራፉን እያሰራጨ ያሉዉ ባንዳዉ መለስና ቡድኑ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በካድሬዎቻቸው አማካኝነት "ዓባይን የደፈረ መሪ"የሚል ቅስቀሳ ማስነገራቸው ይታወቃል።

### ወያኔ ያወጣው አዲሱ የከተማ ቦታን ወደሊዝ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ላለፉት 20 መታት ያጣው ድጋፍ መሠረት ዋናው ምክንያት በከተሞች የሰፈሩት የቀድሞ ሥርዓት ርዝራዦችና በአብላጫኒት ታሪካዊ ጠላቱ አድርጎ የሚቆጥረው የአማራ ህዝብ ነው ብሎ እንደሚያምን በዚህም ምክንያት ይህንን ህዝብ ለመበቀል ሲዝት እንደኖረ ይታወቃል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆኖ የተሾመው ኩማ ደመቅሳ አዋጁ ህግ ሆኖ ከወጣ ቦኋላ የከተማውን ህዝብ ለማነጋገር ሞክሮ ብዙ ተቃውሞ ተነስቶበት እንደነበረ የጠቀሰው ዘጋቢያችን አዋጁ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በተለያዩ ክልሎች ርዕሰ ከተሞችም ተመሳሳይ የሆነ የህዝብ ቁጣና ተቃውሞ እንዳስከተለ ገልጾአል። ይህም በኑሮ ውድነቱና በፖለቲካ አፈናው ምክንያት በነበረው አለመረጋጋት ላይ ተጨማሪ ብሶት ወልዶአል ተብሎአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org